# በሁለት ብር ብድር

ወ/ሮ ገነት በየነ በባሌ ጎባ ከተማ 02 ቀበሌ ነዋሪ ናቸው፡፡የአራት ወንዶች እናት ሲሆኑ ራሳቸውን ለመቻል ንግድ ቢጤ ይሞካክራሉ፡፡ እህል እያመጡ ለቸርቻሪዎች ይሻጣሉ፡፡ በዱቤም 70,000 ብር ለነጋዴዎቹ ይሰጣሉ፡፡ ይሁን እንጂ በዱቤ የሰጡት ብር ቅልጥ ብሎ ይቀራል፡፡ ይህ የሆነው ደግሞ ባለቤታቸውን አዲስ አበባ ለ3 ወር ለማስታመም መጥተው በነበረበት ወቅት መሆኑ ደግሞ ችግሩን የከፋ ያደርገዋል፡፡

መቼም የሰው ልጅ ተስፋ አይቆርጥም፡ እሳቸውም በዚህ ተስፋ አልቆረጡም፡፡



ወ/ሮ ገነት በየነ
በልዩ ሎተሪ የ110,000
ብር ዕድለኛ
ባሌ ጎባ

አንድ ዕለት ለባለቤታቸው ጓደኛ ዕቁብ ይወጣለቸውና የዕቁቡን የፍንጥር ልበልህ ይላቸውና መንገድ ይጀምራሉ፡፡ እሳቸው ብቻችሁንማ አትሄዱም እኔም አብሬያችሁ እሄዳለሁ በማለት የግብዣው ተካፋይ ይሆናሉ፡፡

ህዳር 30 2003 ዓ.ም አለፈ፡፡ ቀናትም ነጎዱ፡፡ለባላቸው የልዩ ሎተሪ ቲኬቱን እንዲያዩላቸው ይሰጣሉ፡፡ የ110,000 ብር ዕድል ለሳቸው መድረሱን ያረጋግጣሉ፡፡ ባለቤታቸው ያቆራረጣቸውን ሁኔታ እንዲህ ያስታውሳሉ፡፡

የፍንጥር ግብዣው ተጧጥፏል፡፡ የሎተሪ አዟሪው አጠገባቸው ሲደርስ ሰለማይወጣ አልገዛም ይላሉ የፍንጥር ጋበዡ

ወ/ሮ ገነት እስቲ አምጣው ለእኔ ይሉና በቦርሳቸው የያዙትን ብር ይቆጥራሉ ስምንት ብር ብቻ ነው የያዙት ድርጊታቸውን የተመለከቱ ባለቤታቸው “በቃ ግምሹን ቁረጪ” ይሏቸዋል፡፡

ለምን ቢደርሰኝስ ብለው ሲመልስላቸው

የያዝሽው ብር እኮ አይሞላም ሙሉ ቲኬት ለመግዛትይሏቸዋል

አበድሩኛ ሁለት ብር ሲሉ ያበድሩቸዋል ዛሬ ያቺ ሁለት ብር ባትኖር ሙሉ ዕጣው አያገኙም ነበር ፡፡ ሙሉ ቲኬት ዕድል ፈንኗን እንካችሁ ብለላች፣